የምፅዓቱ መፅሐፍ ቅዱስ HOLY BIBLE የምሥራች

|ቅጽ 83 ቁጥር 6(978)|

"እግዚአብሔርን ፈልጉት ትጸናላችሁም፥ ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ" (መዝ. 104፡4)

እግዚአብሔር ይመጣልናል!

"ሰማዩን ቀደህ ምነው ብትወርድ ተራሮችም ምነው ቢናወጡ እሳት ጭራሮን እንደሚያቃጥል እሳትም ውሃን እንደሚያፈላ ስምህ ለጠላቶችህ ይገለጥ ዘንድ አህዛብም በፊትህ ይንቀጥቀጡ" ት. ኢሳያስ 64፡1-2

ነብዩ ኢሳይያስ የነበረበት ዘመን እስራኤል ከእግዚአብሔር የራቀበት ወቅት ነበር። የኃጥያትና የግፍ ጽዋ በዝቶ እስራኤል ወደ ምርኮ ልትሰጥ የቀረበችበት ጊዜ ነበር።

በዚያን ወቅት የችግሮችና የጉስቁልናዎች ክምር የበዛበት ሕዝቡ የተከፋፈለበት አንድ ሊሆን ያልቻለበት እጅግ የከፋ መንፈሳዊ በራድነት የሰፈነበት ሁኔታ ነበር። ይህ ዛሬም ይታያል። የእግዚአብሔር ሕዝብ መከራው ሲበዛ ለማያምኑ ክፉዎች ተላልፎ ሲሰጥ "አምላካችሁ የት ነው" የሚባልበት ሁኔታዎች ይበዛሉ።

በእንደዚህ ባለ ሁኔታ ጥንት በብሉይ ኪዳን ጌታ ደቀመዛሙርት ሕይወትም ሲከሰት እግዚአብሔር ነብዩ ኢሳያስን የመሰሉትን ያስነሳል ይጠቀማል።

በእግዚአብሔር አዳኝነት ሥጋ ለባሽ መቆም እስከማይችልበት ድረስ ወዮ እግዚአብሔርን አይቻለሁ። የሚል መደነቅ እስኪመጣ ድረስ ጌታ ለወደዳቸው፤ ለመረጣቸው... ይገልጣል።

እግዚአብሔር ሁኔታዎች በከፉበት በጨለመበት ሰዓት ክንዱን እንደሚያሳይ ፣ የደከሙትን በመንፈስ ቅዱስ እሳት እንደሚነሱ እንደሚያቀጣጥል የነብዩ ኢሳያስ መገለጦችና በአዲስ ኪዳን በሐዋርያቱ አንደታየው በቀጣዮቹ ዘመናትም የእግዚአብሔር ቃል እየተሻገረ በሰው ልማድ በሥጋዊነት የእግዚአብሔር ቤት በተበላሸበት ወቅት ጌታ ምርጦቹን እያነሳ ቤቱን እያደሰ፤ እያቀና ለዚህ ዘመን ደርሰናል።

እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሲባርክ ለሥራው ሲለይ የሚቀድመው ነገር ብርቱ መንፈሳዊ ፍልሚያ እና ለጸሎት በተሰበረ ልብ ጌታን መፈለግ ይሆናል። ዘፍ 32፡24 (ያዕቆብ) ት.ዳንኤል 9፡1-23 ነቢያት ሐዋርያትም ምሳሌዎች ናቸው።

እግዚአብሔር አስነስቶአቸው ለሕዝቡ መትረፍ መዳን መሣርያ ይሆናሉ።

ለማንኛውም ሀገር የተሰፋ ምንጩ የእግዚአብሔር ጉብኝት ነው።

በዓለማችን ላይ የሚገኙ ሀገራት ሁሉ መልካም አስተዳደር እና ፍትህ፤ ብልጽግና እና ሠላም እንዲኖራቸው ሕዝቦች ይመኛሉ፤ ይፈልጋሉ።

የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ደግሞ ሥጋ ለባሽ ሰው፤ ንጉሥ፣ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚንስትር ሳይሆን እራሱ እግዚአብሔር ነው። *1ሳሙኤል 8፡4 መዝሙር 46፡7*

የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን ይህንን በመዘንጋት ወይም ባለመቀበል የሰው መሪ ንጉስ እንዲኖረው በመመኘት ነብዩ ሳሙኤልን ማስጨነቅ በያዘበት ወቅት ነብዩ እጅግ አዝኖ ይህንን ሲቃወም እግዚአብሔር እራሱ የሕዝቡን መሻት ነብዩ እንዲፈጽም ፈቅዶ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በተከታታይ የተሾሙት ነገስታት ብዙ መከራ፣ ሰደት እና ግዞት እንዳደረሱበት መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር ያብራራል። *መዝሙረ ዳዊት 46፡7*

የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚመቸው ባይሆንም ለመንግስት ይታዘዝ ዘንድ ጌታ በቃሉ ያዘዘ ሲሆን እነዚህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመከራ እና ለምርኮ ያበቁ መሪዎች የእግዚአብሔር ዓላማ ማስፈጸሚያ መሆናቸውን ቃሉ ያረጋግጣል። *ሮሜ 13፡1 1ጢሞ 2፡1 መጽሐፈ አስቴር 4፡16*

አንድ ሀገርና ሕዝብ በትክክለኛ መንገድ የሚተዳደሩት፣ የሚጓዙት ተስፋቸውን በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ የእግዚአብሔርን ፊት በተሰበረ ልብ ሲፈልጉ *"በስሜ የተጠሩ ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ፊቴን ቢፈልጉ፣ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢያታቸውንም ይቅር እላለሁ"* 2ዜና 7፡14

በዚህ ቃል መሠረት ይህ የፀሎት ትዕዛዝ በእግዚአብሔር ለተጠሩት ሕዝቦች እና በብሉይ ኪዳን

ምሳሌ ለሆነው የአይሁድ /የእስራኤል ማህበረሰብ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ደግሞ ለክርስቲያኑ ማህበረሰብ ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አሮጌውና አዲሱ የተባሉትን በማነፃፀር አዲስ የተባለውን አንድነት እንድንጠብቅና እንድንለማመድ ታዘናል:: አሮጌው አዳም፣ አዲሱ አዳም፣ አሮጌዋ እየሩሳሌም፣ አዲስቱ እየሩሳሌም፣ አሮጌው እስራኤል፣ አዲሱ እስራኤል *ዘፍጥረት 9:13 ሕዝቅኤል 1:28፣ ራዕይ 4:3*

መንፈሳዊ ተሀድሶ /መነቃቃት የሚያስገኝ ጸሎት

"ከጸለየም በኃላ ተሰብስበው የነበሩበት ሰፍራ ተናወጠ፣ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ምላባቸው የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጽ ተናገሩ" (የሐዋርያት ሥራ 4:31)

ለመንፈሳዊ መነቃቃት የሚደረግ ጸሎት ከሌላው የጸሎት አይነት የተለየ ነው:: ለዚህ አይነቱ ጸሎት ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ መጥቀስ ይቻላል:: ምክንያቱም ውጤታማ ነውና:: ይህን ጸሎት የሚመራው ጌታ እግዚአብሔር፤ ጌታ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን አንድ ብቸኛ ዓላማው ባለቤቱ የሆነለት እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ይህ ጴንጤቆስጤ ወይም ጰራቅሊጦስ የተባለውን የእግዚአብሔር መንፈስ መውረድና መፍሰስን የሚያስከትል የጸሎት ሂደት/ስርዓት ነው:: የመንፈሳዊ መነቃቃት ጸሎት የሚነቀንቅ ልብና መንፈስን የሚነካ የሚለውጥ ውጤት የሚያስገኝ ነው:: ነብዩ ኤልያስ ይህን ፀሎት ተለማምዷል "ይህ ሕዝብ ያውቅ ዘንድ ስማኝ፣ አቤቱ ስማኝ አለ:: የእግዚአብሔር እሳት ወደቀች የሚቃጠለውን መስዕቱንም እንጨቱንም፣ ድንጋዩንም ፣አፈሩንም በላች" ነኛ ነገስት 18:37

በነብዩ እዝራ ጊዜም ይህ መሰሉ ጸሎትና መንፈሳዊ መነቃቃት ተከስቷል:: *"አምላክ ሆይ ሀጢያታችንን ከራሳችን ላይ በዝቶአልና፤ በደላችንም ወደ ሰማይ ከፍ ብሎአልና፤ አምላክ ሆይ አፈራለሁ.... እዝራም እያለቀሰና በእግዚአብሔር ቤት ፊት እየወደቀ በጸለየ እና በተናዘዘ ጊዜ ከእስራኤል ዘንድ የወንድና የሴት እንዲሁም የሕፃናትም እጅግ ታላቅ ጉባኤ ወደ እርሱ ተሰበሰበ፤ ሕዝቡም እጅግ አለቀሰ:: ከአምላካችን ጋር ቃል ኪዳን እናድርግ እንደ ሕጉም ይደረግ::"* ዕዝራ *9:6፣ 10:3*

የሐዋርያት ሥራ 4:24-29 በብርቱ ጸሎት የመንፈሳዊ መነቃቃት በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ መከሰቱን ያብራራል:: *"እነርሱም በሰሙ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ፦ እንዲህም አሉ "ጌታ ሆይ አንተ ሰማዩንና ምድሩን፤ ባህሩንም በእነርሱም ውስጥ ሁሉ ያሉትን የፈጠርህ በመንፈስ ቅዱስም በብላቴናህ በአባታችን በዳዊት አፍ አሕዛብ ለምን አሰቡ? የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በጌታና በተቀባው ላይ አብረው ተከማቹ ብለህ የተናገርህ አምላክ ነህ::"* ከጸለየም በኃላ ተሰብስበው የነበሩበት ሰፍራ ተናወጠ፣ በሁሉም ላይ መንፈስ ቅዱስ ምላባቸው፤ ቃሉንም ተናገሩ::"

ለመንፈሳዊ መነቃቃት የሚደረጉ የልዩ ልዩ ጸሎቶች ባህሪያት:-

1. **የመንፈሳዊ መነቃቃት ጸሎት በከፍተኛ መቃተት እና በለቅሶ ይካሄዳል ዘፀ 2:24 ነሳሙ 12:18**

እግዚአብሔር ወደ እርሱ የሚቀርቡትን ይደርስላቸዋል፣ ይታደጋቸዋል:: *"ጽዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆችዋን ወልዳለችና" ኢሳያስ 66:8*

እንዲሁም ደግሞ *"መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል"* ሮሜ 8:26

በግንቦት 1983 ዓ.ም በሀገራችን የተካሄደ ጸሎት ከፍተኛ እልቂት አስቀርቷል::

2. **የመንፈሳዊ መነቃቃት ጸሎት የአስደናቂ እና አስገራሚ ጸሎት ውጤት ነው::**

ነብዩ እዝራ በነበረበት ኃጢያት እጅግ ማፈሩን፤ መፍራቱንም በገለፀበት ወቅት በፍፁም ንስሀ ወደ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይዞ እንደቀረበና እግዚአብሔርም እንደጎበኛቸው ጽፏል:: ዕዝራ 9:6 እግዚአብሔር እንዲህ ባለ የተሰበረ ልብ የሚደረግን ጸሎት እንደሚመልስ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና የቤተክርስቲያን ታሪክ ያረጋግጣሉ:: ...

3. **የመንፈሳዊ መነቃቃት ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መውደቅን የተከተለ ብርቱ ፀሎት ነው::**

ጌታ ይህን በጌቴሰማኒ ጸሎቱ አስተምሮናል ማቴ 26:39

4. **የመንፈሳዊ መነቃቃት ጸሎት ሰዎችን የሚዎዥ /የሚያድን/ ጸሎት ነው::ሮሜ 8:32**

እግዚአብሔር አንድያ ልጁን አሳልፎ የሰጠው በእርሱ ያመነ ሁሉ ከቁጣና ከዘላለም ሞት እንዲድን ነው::

5. **የመንፈሳዊ መነቃቃት ጸሎት በቃል ኪዳን ላይ የተመሰረተ ነው::**

እግዚአብሔር ለሕዝቡ በየዘመናቱ ቃል ኪዳን ይገባል:: የአዲስ ኪዳን ቃል ኪዳኑ ደግሞ ከሁሉ የበለጠና የማይሻር ቃል ኪዳን ነው:: በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት ሕዝቡ ወደ እግዚአብር በሚፀልይበት ወቅት እግዚአብሔር ይሰማል:: ት. ኢዩኤል 2:28 ማቴ 28:20

6. **የመንፈሳዊ መነቃቃት ፀሎት የህብረት ጸሎት ነው:: 2ኛዜና 7:14**
7. **የመንፈሳዊ መነቃቃት ጸሎት ራስን የሚያስክድ እኔነትን የሚያጠፋ ጸሎት ነው:: ዘፀ 32:32**

ለሀገራችን መንፈሳዊና ሥጋዊ እንቆቅልሽ ሰቆቃዎች መፍትሄ በእነዚህ የመንፈሳዊ መነቃቃት የጸሎት ባህሪያት በመትጋት የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ ሆነን ሕዝባችንን እንታደግ::

ተስፋ በጨለመበት ወቅት ጸሎት የተስፋ ብርሃን ያቀዳጃል::

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተፃፈልን በቤተክርስቲያን ታሪክ እንደተገለጠው በእራሳችንም ሕይወት ያየነውን፤ ያለፍንበትን የምንመሰክረው ተስፋ የሚሰጥ በጠፋበት ወቅት ልዩ ተስፋን የሚያስገኝ በእውነተኛ ልብ ለእግዚአብሔር የሚደረግ ጸሎት ነው::

እግዚአብሔር ከምድራዊ ግፈኛ ዳኞች የተለየ እጅግ አዛኝ የተበደሉትን የተጎዱትን የሚሰማ መሆኑን ጌታ የመበለቲቷን ሴት ከክፉ ዳኛ ያገኘችውን ፍትህ ከራሱ ዘላለማዊ ቅን ፍትህ ጋር በማነፃፀር ያቀረባል:: ያቺ መበለት ሴት ሳታቋርጥ ለዚያ ክፉ ዳኛ አቤቱታዋን እንዳቀረበችው እኛም ሳንታክት በእውነተኛ ልብ ጌታን በፀሎት ብንጠይቀው መልስ እንደምናገኝ፤ ተስፋችን እንደሚመለስልን ያስተምር ነበር::

"ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንደሚገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፤ እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮሁ፤ ለሚታገሳቸው ምርጦቹ ላይፈርድላቸውምን? እላችኋለሁ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል::" ሉቃስ 18:1-8

ጌታችን ከነዓናዊት ሴት ልጅን ከአጋንንት እስራት እንዲፈታት በተማፀነችው ወቅት የተናገረው የምጸት ቃልና የሰጣት የፈውስ ምላሽ እንዲሁ እኛም እራሳችንን ዝቅ በማድረግ በትህትና እንድንጠይቀው ሊያስተምረን ነው:: ማቴዎስ 15:28

ጌታ በዘር ትምክህታቸው ለሚመጻደቁት አይሁድ ይህንን ምሳሌ ያቀረበው በሚገባቸው መልኩ ሌላውን የሚንቁ ራሳቸውን ከሌላው ዘር የተሻለ አድርገው ለሚቆጥሩ የተሰጠ ታላቅ የተባለው መልዕክት እንጂ ጌታ ሰዎችን በዘር የማያበላልጥ ሥራውና ሕይወቱ ቃሉም ያረጋግጣል::

በመታመን የሚደረግ ፀሎት ፍሬያማ ነው

"ከእንግዲህ ወዲህ ሊታለቅሰም፤ በጩኸትም ድምጽ ይራራልሃል፤ በሰማህም ጊዜ ይመልስልሃል" ኢሳይያስ 30:19

እግዚአብሔርን በመታመን በቅን ልቦና የምናደርገውን ፀሎት እግዚአብሔር ይመልስልናል:: እግዚአብሔር ሕዝቡ ሲለምነው (ልመና ሲያቀርብ) እንደሚመልስ በቅዱስ ቃሉ የተነገረውን በማመን ልንፀልይ ይገባል:: ወላጆች የልጆቻቸውን ልመናና ጩኸት ከሚሰሙት በላይ እግዚአብሔር የአማኝ ልጆቹ ጩኸት ይሰማል ሮሜ 8:32

ጸሎታችንን ለእግዚአብሔር በምናቀርብበት ወቅት እንደሚሰማን እና እንደሚመልስልን ታምነን እናቀርባለን:: የገጠመንን ችግር፣ ኃጢያት፣ ጉስቁልና ደብቀን በመያዝ መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም እንዲገልጽልን በመማፀን ወደ እግዚአብሔር ፀሎታችንን ብናቀርብ ጌታ እግዚአብሔር ይመልስልናል::

እግዚአብሔር በምህረት የተሞላ ጌታ በመሆኑ በደላችንን በመናዘዝ ምህረቱን ብንጠይቅ እሱ ይምረናል:: ከገባንበት ውጥንቅጥ ችግርም ያወጣናል:: ኤፌ 2:4

በጸሎት ለጌታ የምናቀርባቸው ጉዳዮች የቱንም ያህል ጊዜ ቢወስድ እግዚአብሔርን ሳንታክት እንጠይቀው በመሰላቸት ጸሎታችንን አናቋርጥ፤ አናቁም:: እርሱ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን የሚያውቅ ሳንጠይቀው የሚመልስ ቸር አምላክ መሆኑን አምነን ጸሎታችንን እናቅርብ::

"እንዲህም ይሆናል፤ ሳይጣሩ እመልሰላቸዋለሁ፤ ገናም ሲናገሩ እሰማቸዋለሁ::" ኢሳ 65:24

"እግዚአብሔር ቸር፣ ምህረቱም ለዘላለም፣እውነቱም ለልጅ ልጅ ነውና::" መዝ 99:55

"የኃጢያታችን ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ፣ ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጎበኘበት በአምላካችን ምህረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው::" ሉቃስ 1:78

እግዚአብሔር ጸሎቻችንን የሚሰማውና የሚመልስልን ከእርሱ ደግነትና ምህረት የተነሳ መሆኑን በማመን በፍሬያማ ጸሎት እየተጋን በረከቱን እንቀበል::

የእውነተኛ ጸሎት ልዩ ምልክት ጌታን ማወቅና ማክበር ነው::

ሰዎች የሚያከብሩትን ሰው ለመስማት ለመታዘዝ ዝግጁ ከመሆናቸው እጅግ በበለጠ ሁኔታ ጌታ የሚያከብሩትን ልጆቹን ጸሎት ለመመለስ ዘወትር የተዘጋጀ ነው::

እግዚአብሔርን ሳይሆን የሰዎችን ክብር እና ክፉ ግብዝነት በእግዚአብሔር ጉባኤ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጸሎት መልስ ሳያገኝ የእግዚአብሔር ሕዝብ ምሳሌ የሆነው የእስራኤል ሕዝብ 400 ዓመታት በግብጽ ባርነት 70 ዓመታት በባቢሎን ምርኮ ለመማቀቅ ተዳርጓል::

"ስለዚህ ሕዝቤ ወደ ምርኮ ሄዱ ጌታን አላወቁትምና" ኢሳ 5:13

እውነተኛ ጸሎት እውነተኛውን አምላክ በማክበር ሌሎች አማልዕክት አይኑሩህ የሚለውን ትዕዛዝ የተከተለ ነው:: ዘጸ 20:3

ሌሎች አማልዕክትን አላመልከም ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለኝም ብሎ ለነፍሱ ያልሳሳውን ነብዩ ዳንኤልን ጌታ ከተራበ ከአንበሳ አፍ አድኖታል:: *"ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ ሰዶም አጸልይና አለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደ አምላክ አጸናሁ:: (ዳንኤል 9:3)*

ትክክለኛ የእግዚአብሔር ሰዎች የሚለዩባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ ለጌታ ያላቸው ሽክምና ፍርሃት ነው:: ሰዎች መከራን እና ሞትን ከምንፈራበት በጣም የተለየ እግዚአብሔር የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ያለው ቅዱስ ፍርሃት ነው:: ምሳሌ 1:7

በእንደዚህ ያለ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፍርሃት የተሞላው ነብዩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ክብር ባየ ጊዜ ወየሁ ጠፋሁ ብሎ ይንቀጠቀጥና እግዚአብሔር ማንን ልላክ ብሎ ሲጠይቅ፤ እኔን ላከኝ በሚል የእግዚአብሔር አክብሮት ኃይል መልዕክተኛና የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት የብሉይ ኪዳን ወንጌላዊ የሚባልለትን ትልቅ መልእክት ድንግል እንደምትጸንስ የወለደችው ክርስቶስ መሲህ አምላክ መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የፃፈልን ነው:: ኢሳ. 6:3-9

አማኞች በዚህ የእግዚአብሔር አክብሮትና ቅዱስ ፍርሃት ተሞልተን ሰዎችን ለማዳን ሥራ ተጠርተናል::

የእግዚአብሔር ካህናት ሆነን ለእግዚአብሔር ጸሎት እናቅርብ

የብሉይ ኪዳን ካህናት ሥራ ለእግዚአብሔር አገልግሎት በመለየት ሕዝቡን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት መቆምና የሕዝቡን ኃጢያት ማሳወቅ ከእግዚአብሔር ምህረትና በረከቱን ሕዝቡ እንዲያገኝ ማድረግ ነው::

ይህ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ተወካይ ተጠሪ በመሆን ለጌታ ምልጃ ጸሎትና ምስጋና የማቅረብ አገልግሎት በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ያለ አማላጅም ተማላጅም በሆነው በሊቀ ካህናችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጀመረ ለእኛ ለአማኞች ሁሉ ንጉሥ ካህን በሚል የተሰጠን ሀላፊነትና መብት ነው:: *"በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሰዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ:: 1ኛ ጴጥሮስ 2:5*

የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ነገር የምንጠይቅ የምንፀልይ ከሆነ ጌታ ይመልስልናል:: *"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፣ እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል:: የምንለምነውንም ሁሉ እንደሚሰማን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን::"* 1ዮሐ 5:14

እያንዳንዱን አዲስ ቀን በጌታ ፊት በመሆን በንሰሀና በምስጋና ብንሞላ እግዚአብሔር ፀሎታችንን ይሰማናል፤ ምድራችንንም ይፈውሳል:: *"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፣ እንደፈቃድ አንዳች ብንለምን ይሰማናል::"* 1ዮሐ 5:14

እግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ ልጁን ለዚህ ከፍ ያለ ኃላፊነትና ጥቅም ስለሰጠው ስሙ የተመሰገነ ይሁን አሜን::

በክርስቶስ ባለን እምነት ከእግዚአብሔር ያገኘነውን ኃላፊነት በማስተዋል እንፈጽም:: በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆነው የአማኝ ልጆች ልብ ነውና:: ይህን ልባችን እንደንጉስ ካህን እንጠቀምበት:: የተሰጠን እድል ልዩና ከፍተኛ ስለሆነ አማኞች እርስ በእርሳችን መታመንን እናረጋግጥ:: ለፍቅር፣ ለሕብረት፣ ለስልጣኔ፣ ለሰላም ድርድር እምቢ የሚሉትን የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች ምሳሌ አንከተል:: የእግዚአብሔር ሕልውና የተከሰተባቸው አንድ አምላክ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን እንታዘዝ::

የጸሎታችን መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ነው::

የክርስትና እምነትና ጉዞ እውነትና ሕይወት ዘላለማዊነትን በሚያጎናጽፈው የእግዚአብሔር ቃል ላይ መመስረት ይኖርብናል::

"በስሜ የተጠሩት ሕዝቦቼ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ፣ፊቴንም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፤ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ ኃጢያታቸውንም ይቅር እላለሁ፣ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ:" ነኛዜና 2:7-14

"ለምኑ ይሰጣችሁማል፣ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋል" ማቴ 7:7

በእግዚአብሔር መንፈስ በእግዚአብሔር ቃል የሚቀርብ ጸሎትን እግዚአብሔር እየመለሰ ልጆቹን ከክፉ እየመለሰና እየጠበቀና ሌሎችንም ጭምር የሚታደገው እግዚአብሔር የደነገገው የጸሎት ሥርዓት ነው:: ይህ ጌታ ለሕዝቡ የገባው የማይሻር ቃል ኪዳን ነው::

ብዙዎች እምነት ከጥልቅ ስሜት ብቻ የተያያዘ አድርገው ቢገምቱም የክርስትና እምነት መሠረቱ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው::

ከእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ሕዝብ የአተለየ ለግብጽ ባርነት የባቢሎን ምርኮና በክርስትና የጨለማ ዘመን ስም ብቻ በያዙት ዘንድ የሚታይ የክርስቶስ ቃል የጠፋበት የብርሃን ሥራ ሳይሆን የጨለማ ሥራ የተገለጠበት መካከለኛው ዘመን ተከስቷል::

ክርስቲያኖችን የሚያስነቅፍ ዘረኝነት፣ የገንዘብ ፍቅርን የኃጢያት ሁሉ ሥር የተባለውን የተከተለ ስብከትና የሕይወት ልምድ ይታያል:: ይህን ከፉ መንገድ የሳተ አሰራር ለመመለስ ለማቅናት እግዚአብሔር ከጥንት አልቃሽ ነብያትና ሐዋርያት መካከል በመጨረሻው ዘመን የተሀድሶ አስተማሪዎችን፤ ቀጥሎም የእውነተኛ መንፈሳዊ መነቃቃት ሰባኪዎችን ሲያስነሳ፤ ሲጠቀም እናያለን::

"ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቶአል::" ሆሴዕ 4:6

"ባድማ የነበሩትን ይሰራሉ ከቀድም የፈረሱትን ያቆማሉ፣ ... እንደገና ይሠራሉ" ኢሳ 61:4

በጸሎት መንፈሳዊ ተሀድሶ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሳተበት ከኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከፉ ልምምድ ይመለሳል:: በመንፈሳዊ መነቃቃት ደግሞ ጌታ ሕዝቡን እያነቃቃ ዓለምን በምስራቹ ወንጌል በአማኞች ይደርሳል::

የቤተክርስቲያን ምስረታና የዘመናት ጉዞዋ በጸሎት ነው::

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው የመሠረታት የሕዝቡ ማህበር የተዋቀረችው በእግዚአብሔር ቃል በተመሠረተ የጸሎት ልመና ሲሆን በአዲስ ኪዳንም ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በእግዚአብሔር መንፈስ ሕዝቡ የደረሰበትን ሰቆቃ የተማመኑበት መሲህን ማጣት ባስከተለው ብርቱ ጸሎት ነው:: የአቤል ደም ጩኸት ወደ ጌታ ፊት ደርሷል:: ዘጸ 4:10

የእግዚአብሔር ሕዝብ በባርነት ምድር ጩኸት ወደ ጌታ መድረሱ፤ (ዘጸ 2:23) የእግዚአብሔር ሕዝብ በእውነተኛ ልብና ጸሎት ለእግዚአብሔር ማቅረብንና መመለሱን ያሳያሉ::

በአዲስ ኪዳን ለእግዚአብሔር ሕዝብና ለመላው ዓለም መዳን የሆነው መሲህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር አገልግሎቱ ያስተማረውና በመከራውና ከሞቱ በኃላ በትንሳኤ ከማረጉ በፊት ያስተማረው በሐዋርያቱም በጭንቅና በመከራ ወቅት ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው የእግዚአብሔር መንፈስ በብርቱ ጸሎት የፈጸመችው ዘላለማዊ ሥራዎች ናቸው:: ማቴ 26:3 ሉቃ 22:42 ሐዋ 2:3 በአስደናቂ የእግዚአብሔር

ታምራት ቤተክርስቲያን ስታገለግል ሐዋሪያቱ ድንቅና ታምራት ሲያካሄዱ ክፉ ሰይጣን ጣልቃ ገብቶ ቤተክርስቲያን የቄሳርን መንገስት መሳሪያ በሆነችበት የመጀመሪያው የውድቀት ዘመን ይህንን ክፉት በመቃወም የተነሱ ቅዱሳን ሰማዕታት የበረቱት በጸሎት ነው::

በመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በአውሮፓ ከዚያ ቀድሞ በሀገራችን ኢትዮጵያ እና ደቂቀ እስጢፋኖስ ለክርስቶስ ብቻ ስግደት አምልኮ በሚል እስከ ሞት የተሰውት በጸሎት ተጋድሎ ነው::

ታላላቆቹ መንፈሳዊ መነቃቃቶች በአውሮፓና በአሜሪካ በአፍካና በእስያ በመላው ዓለም የተዛመቱት በጸሎት በጌታ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው::

ዛሬም የሀገራችንና የዓለም እንቆቅልሽ የሚፈታው በእግዚአብሔር መንፈስ በጸሎት ብቻ ነው::

የጸሎት ጎብረቶች የእግዚአብሔር ቤቶች ናቸው

"ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች (ማቴዎስ 21:13)

የቤተክርስቲያን ራስና መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ብሎ ያስተማረው በእግዚአብሔር ቤት በቤተመቅደሱ ነጋዴዎችና አትራፊዎች የግላቸውን ንግድ እያጧጧፉ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ጸሎት በመከልከሉ ነበር::

በዚህ ዘመን ጌታችን ወደ አብያተክርስቲያናትና አገልግሎት የሚል ስም በያዙት ሁሉ ዘንድ ቢመጣ በዚህ ምድር ከነበረበት ወቅት በከፋ ሁኔታ ቤቱ መቆሸሹን ይረዳል::

በዚህ የእግዚአብሔርን ቤት ባቆሸሸ ክፉ እርም የተያዙት ያለምንም ይሉኝታ ይህን ንግዳቸውን በማስፋፋት ብዙዎች በወንጌል እንዲድኑ ሊውል የሚገባውን ጊዜና ገንዘብ ለሰዎች የስልጣን የጥቅምና የዝና ፍጆታ እያዋሉ ያለምንም ሀፍረት የእግዚአብሔር ሥራን እንሠራለን የሚሉበት ዘመን ላይ እንገኛለን:: በከበሩት ሀብታም ሀገሮች ብቻ ሳይሆን በድሀ ሀገሮች ሳይቀር የጌታ ስም መናገጃ ሆኗል::

የዘመናችን የቤተክርስቲያን ሻጮችና ነጋዴዎች በእምነት እንቅስቃሴ ስም ምን ያህል ከቡር የወንጌሉን ስም እንዳስነወሩ ከየሚዲያው ከሚሰማው በላይ በያለንበት ማኅበር ይህ ክፉ እርም ታላቆች በተባሉት ሳይቀር ሰፍኖ ይገኛል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ጌታ ነውና:: (እብራውያን 13:8) በክርስቶስ መንፈስና በቃሉ እነዚህን ገበታ ለዋጮች፤ ምንደኞች፤ አታላዮች እናጋልጥ:: መንጋውን ከእነዚህ አሳቾች እናድን:: "ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ ይልቁን ግለጡት" (ኤፌሶን 5:11)

የወንጌል አገልግሎትና የጎብረቶች ተዋጽኦ

በብሉይ ኪዳን ስለ ሰው ዘር መፈጠር ውድቀትና የመጨረሻው ተስፋ ከተጻፈበት ጀምሮ ባለው ሂደት የጎብረቶች ተዋጽኦ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ነው:: (ዘፍ. 1:26፣ 1 ዮሐንስ 1:3)

እግዚአብሔር ከልዩ ፍቅሩ የተነሳ ከመልካሙ መንገድ የወጣውን የሰው ዘር ለመመለስ "ወዴት ነህ?" ብሎ ከጠየቀበት ወቅት ጀምሮ ሊያድነው ሊመልሰው ብዙ እቅዶችን አሠራሮችን የፈጠረው በህብረት ማዳኑን በማሳየትና በመጨረሻም እራሱ አምላክና ሰው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል መከራ፣ ሞቱ እና ትንሳኤው የሰውን ዘር ያዳነው ባዘጋጀው የእግዚአብሔርና የሰዎች ጎብረት መርህ በመስጠት ነው:: (መዝሙረ ዳዊት 99:5)(ዘፍ. 3:4)

የእግዚአብሔር የማዳንና የምህረቱ ብዛት ለሕዝቡ የደረሰውም የሕዝቡን ልዩነቶች በቅዱስ መንፈሱ በማስተካከል በተገኙት መለኮታዊ ጎብረቶች ነው:: (መክብብ 4:9፣ መዝሙረ ዳዊት 132:1፣ ሐዋርያት 4:31)

በዚሁ የእግዚአብሔር የጎብረት አሰራር ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ላይ ከተመሠረተች ጀምሮ እግዚአብሔር በረከቱን ማዳኑን መመለሱን ማደሱን በጎብረቶች ቀጥሏል::

እነዚህ ጎብረቶችን ለማጥፋት ለማሳሳት ሠይጣን ዓለምና ሥጋ ሁልጊዜም ቢጥሩም እግዚአብሔር በቅዱስ መንፈሱ ዛሬም ድረስ እስከፍጻሜው የሰዎችን ቅዱስ ጎብረት እንደተስፋ ቃሉ እየጠበቀ ያጸናል በመጨረሻም በአንድ ላይ በዘላለማዊ ቤቱ ይሰበስባል፤ ሃሌሉያ (ራእይ 7:9)

ለየምጽአቱ የምሥራች የተሰጡ ጎብረቶችና ወገኖች

የምጽአቱ የምስራች የወንጌል መነቃቃት በሀገራችን ኢትዮጵያ ከታሰበበት ወቅት ጀምሮ ጌታ የተጠቀመባቸው ጎብረቶች ሊዘከሩና ሊከበሩ ይገባል::

ይህ ጋዜጣ የእንግሊዘኛውን እትም አንብበው ጥያቄውን በ1980 ዎቹ መጀመሪያ ላይ አሜሪካን ሀገር ላለው ዋና አሳታሚ የላኩት የአዲስ አበባ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የሠንበት ተማሪዎች ይዘከራሉ::

ከዚያም ትርጉሙን ተጠይቆ የጀመረው ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ የወጣቶች ጎብረት የአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ተጠቃሽ ይሆናል:: በመቀጠልም ተርጓሚውን የደገፉ እና የተባበሩ የንግድ ሥራ ኮሌጅ ምሩቃን ጎብረት የቃለ እግዚአብሔር አንባቢዎች ጎብረት ብድራት ሲታሰብ ይኖራል::

"በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ ሊያደርግ ለሚቻለው ... በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን::" (ኤፌሶን 3:21)

ልዩ ምስጋና

በዚህ ዓመት የምጽአቱ የምሥራች 34ኛ ዓመት ክብረ በዓል እንዲካሄድ አዳራሽ በነፃ ያከራዩን የሰሜን ሙሉ ወንጌል አማኞች ማኅበርን ከልብ እናመሰግናለን:: ጌታ አምላክ ይባርካቸው:: በቤተክርስቲያን ደረጃ ብቸኛው ለጋሽ የናዝሬት አማኑኤል ከ25 ዓመታት በፊት ስለሰጡን 500 ብር የምስጋና ትዝታ እናቀርባለን::

የምጽአቱ የምሰራች አገልግሎት

ዓለም አቀፍ የጸሎትና የምስጋና ርዕሶች

<u>ከጋና ምዕራብ አፍሪካ</u>

ላለፉት 20 ዓመታት የምጽአቱ የምሥራች በመላክ ሕይወቴ እንዲለወጥ እንዲስተካከል ለረዳኝ አገልግሎታችሁ ጌታ የተመሰገነ ይሁን::

<u>ከኬንያ /ምስራቅ አፍሪካ/</u>

የምጽአቱ የምስራች ወደ ጸሎት ቤት መሄድ በማልችልበት ወቅት የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ሆኖ እያገለገለኝ ይገኛል:: ህይወቴ በእግዚአብሔር ቃል እንዲሞረድ ጋዜጣችሁ ብዙ ጠቅሞኛል:: እጸልይላችኋለሁ ተባረኩ::

<u>ከኤርትራ /ምስራቅ አፍሪካ/</u>

የምጽአቱ የምስራች በዚህ ላለነው ክርስቲያኖች ትልቅ መድንነትን እያስገኘልን ይገኛል:: ጌታ አምላክ አገልግሎታችሁን ይባርክ::

<u>ከፍሎሪዳ /አሜሪካ/</u>

የምጽአቱ የምስራች ርዕሶች ወቅታዊና ልብን የሚያደርሱ የጌታ መልዕክቶች ናቸው:: ለአገልግሎቱ በሚቀጥለው ወር ስጦታዬን እልካለሁ እግዚአብሔር ይባርካችሁ::

<u>ከጂንካ /ደቡብ ኢትዮጵያ/</u>

የምጽአቱ የምስራች ሥፍራ ሳይወስናት የምታደርስ የክርስቶስን መልእክት በሩቅ ገጠር ላለነው የምታደርስ የጌታ በረከታችን ናት:: ጌታ አገልግሎታችሁን ሕይወታችሁን ይባርክ::

<u>ከአስተባባሪው</u>

በየጊዜው ለምትልኩልን የጸሎት ድጋፍና የማበረታቻ መልእክት ለሁላችሁም ለመመለስ ጊዜና አቅም ስለሌለን በዚሁ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን:: ለአገልግሎቱ ብቸኛው ገቢ የአንባቢያን መዋጮ በመሆኑ ባላችሁበት ሀገር በፓስታ መላኪያ ድጋፋችሁን ጸሎታችሁን በጌታ ስም እንጠይቃለን::

የምጽአቱ የምስራች
Amharic Herald, Addis Ababa, Ethiopia
P.O.Box/የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ

መልዕክት ከየምጽአቱ የምስራች አስተባባሪ

የምጽአቱ የምስራች በሚል መጠሪያ የእንግሊዝኛውን Herald of His coming እየተረጎምን በአማርኛ አንባቢዎች ከ1983 መጋቢት ወር ጀምሮ እንድናቀርብ ያስጀመረን እና ያስቀጠለንን ጌታ የተመሰገነ ይሁን::

የትርጉሙን ሥራ ለመጀመር መነሻ የሆነውን በአዲስ አበባ ቅድስት ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ወንጌሉን በደራሲ ደረሰ ብሩና በመሠሉት የሰሙ የሰንበት ተማሪዎች ለእንግሊዝኛው አሳታሚ ባቀረቡት ጥያቄ ተርጓመው ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ የመጀመሪ ትርጉሙን በአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ የወጣቶች መነቃቂያ በማቅረብ ባገኘው መልካም ምላሽ ነበር::

የትርጉሙ ሥራ በንግድ ሥራ ኮሌጅ ህብረት ቀጥሎ በዛሬው ወቅት ወደ ሶስት ሺህ የሚጠጉ ተከታታዮች በኢትዮጵያና በዓለም ዙሪያ ጋዜጣው በነፃ እየደረሳቸው ይገኛል። ለዚህ ክብር ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን።

በምጽአቱ የምስራች ከሰሜን አዲግራት እስከ ደቡብ አላባ ቁሊቶ ጂንካ ድረስ ጌታን ያመኑ ወደ ሕይወት የተመለሱ አያሌዎች ይገኛሉ።

በቅርቡ በኢትዮጵያ አዲስ ዓመት 2017 ጀምሮ በሀገር ቤት መታተም በመጀመሩ ክብሩን ለጌታ እንሰጣለን። የተባበሩትን ሁሉ እናመሰግናለን። በዚህ አገልግሎት በበጎ ፈቃድ የተሳተፉትን ሁሉ እያመሰገንን አንባቢዎች ወንጌሉ ለህዝባችን እንዲደርስ መዋጮ የአቅማችሁን በፓስታ ቤት ትልኩልን ዘንድ በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን።

የመዳን መንገዶች

1. ለእግዚአብሔር ኃጢያተኛ ስለመሆናችሁ ተናዘዙ "ሁሉ ኃጢያትን ሠርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል" (ወደ ሮሜ ሰዎች 3፡23)
   "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው" (ወደ ሮሜ ሰዎች 6፡23)
2. በኃጢያታችሁ በመጸጸት እግዚአብሔርን ይቅርታውን ጠይቁት " ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል (ትንቢተ ኢሳይያስ 55፡7)
3. ክርስቶስ ኢየሱስ ለኃጢያታችሁ መከራ ተቀብሎ መሞቱን መነሳቱንና ማረጉን በማመን ስለእርሱ ለመመስከር በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ወደሚያጠምቁ ማኅበር ተቀላቀሉ። (ማቴዎስ ወንጌል 28፡19)

እጅግ ብዙ የተስፋ ቃል ኪዳን ጸሎት

ለኢትዮጵያ

በጥንታዊ መጽሐፍትና በታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ የተጠቀሰች ሀገራችን ኢትዮጵያ ያለችበት መከራ ሰቆቃ አልፎ ጌታ የገባላት ቃል ኪዳን እንዲፈጸም። "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"

እንጸልይ፤ እንምከር፤ እንትጋ! (መዝሙረ ዳዊት 67፡31)

ሔዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ አስተባባሪ

የምጽአቱ የምስራች የወንጌል መጎቃቃት አገልግሎት አርትኦት - Tesema Translationa and Related works-
ሥርጭት ብርሃኑ ጥርሰማ
ታይፕና ቅንብር : አቤኔዘር የጽሕፈት ሥራ
አዲስ አበባ
የፓ.ሣ.ቁ 8986
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

Printed by Central Printing Press
Tel. +251-11-466 5781/82